


ራዕይ ለኢትዮጵያ፣

የኢትዮጵያ የድንበር ኮሚቴ፣

የጠለምት አማራ ማንነት ድጋፍ ኮሚቴ፣

## <u>የሰብአዊ መብት ድርጅቶች የጋራ መግለጫ</u>

## <u>ማንነቱንና ርስቱን አሳልፎ የሚሰጥ ትውልድ ኖሮም አያውቅ፣ አይኖርምም!</u>

“ሆድ ሲያውቅ ዶሮ ማታ” እንዲሉ ወልቃይት፣ ጠገዴ፣ ጠለምት፣ ራያ የማነው? የሚለው ጥያቄ ጊዜው ያለፈበት ጥያቄ የሚያደርገው መልሱ በሁሉም ዘንድ የታወቀና የተመሰከረለት መሆኑ ብቻ ሳይሆን ዛሬ ህዝባችን ለዘመናት ባደረገው መራራ የህልውና ትግልና በከፈለው ክቡር መስዋዕትነት ከትህነግ/ወያኔ ወረራ ነፃ የወጣና በልጆቹ እየተስዳደረ የሚገኝ በመሆኑ ጭምር ነው።

ትህነግ/ወያኔ ፀረ-አማራና ፀረ-ኢትዮጵያ ፋሽስት ቡድን ስለሆነ በወረራ በያዛቸው የአማራ አካባቢዎች ቀደምት ነዋሪ የነበረው የአማራ ህዝብ ላይ በጭካኔ የተሞላ የዘር-ማፅዳትና የዘር-ማጥፋት ወንጀሎች ፈፅሟል። የዚህ ፋሽስት ቡድን መገለጫና የጭካኔው መጀመሪያና መጨረሻ በወልቃይት፣ ጠገዴና፣ ጠለምት ወገኖቻችን ላይ የፈፀመው የዘር ማፅዳትና ማጥፋት ወንጀል ነው። በ1972 ዓ.ም ተከዜን ተሻግሮ የአማራን ዘር ለማጥፋት በወልቃይት የጀመረው ጭካኔውና ፀረ-ሰላም ጉዞው በውድቀቱ ዋዜማ ከ 1,600 በላይ የሆኑ ሰላማዊ የአማራ ተወላጆችን በጀምላ ማይካድራ ላይ ጨፍጭፎ የ 40 ዘመን የጭካኔ ታሪኩን በጦር ወንጀል የአማራ ዘር ማጥፋት ወንጀል በመፈጸም ደምድሟል። ይህንንም እውነታ የጎንደር ዩኒቨርሲቲ የጥናት ቡድንና መሰል ተቋማት ባደረጉት ጥናት ግህንብ ከተባል የወልቃይት በረሃ የአማራ ተወላጆች የጅምላ መቃብሮችን በማግኘት በምርምመራው አረጋግጧል። በቅርቡም የማይካድራውን የዘር ፍጅት አስመልክቶ፣ የፌደራል መንግስቱ አቃቢ ህግና ፖሊስ ኮሚሽን ባወጡት ሪፖርት ከ1,600 በላይ በሚሆኑ የአማራ ተወላጆች ላይ ትህነግ/ወያኔ የጀምላ ጭፍጨፋ እንደፈፀመ አረጋግጠዋል።

የወልቃይት ጉዳይ የፍትህ ጉዳይ ነው! የወልቃይት ሕዝብ ጥያቄ የአማራ ማንነት ጥያቄ ነው! የወልቃይት ሕዝብ ጥያቄ ለኢትዮጵያ አንድነትና ሉዓላዊነት የተከፈለ የ 40 ዓመታት ሰቆቃና ግፍ መቋጫ ጥያቄ ነው! የወልቃይት ጥያቄ ኢትዮጵያ ሀገራችን በትህነግ/ወያኔ ለተቀበለችው መከራና ፍዳ ሁሉ መቋጫ ጥያቄ ነው! የወልቃይት ጥያቄ የአማራ ወጣቶች “ወልቃይት ብረሳሽ ቀኜ ትርሳኝ” እያሉ ደረታቸውን ለፋሽስቱ ትህነግ/ወያኔ የጥይት አረር የሰጡለት የፍትህ ጥያቄ ነው!

ይሁን እንጂ “የዘገዬ ፍትህ እንደተከለከለ ይቆጠራል” እንዲሉ ዛሬም ድረስ የወልቃይት፣ የጠገዴ፣ የጠለምት፣ የራያ ህዝብ አማራዊ ማንነት ጥያቄ በጠቅላይ ሚኒስተር አብይ አህመድ አገዛዝ ፍትሃዊ ምላሽ ተነፍጎት ይገኛል።

“ዕርስት በሺ አመቱ ለባለቤቱ” እንዲሉ የወልቃይት ህዝብ የአማራ ማንነት ጥያቄ አወዛጋቢነቱ ያከተመው ወራሪው ሃይልና ጀሌው ወልቃይትን ለቆ ወደ መጣበት ከፈረጠጠ ከህዳር 2010 ዓ.ም ማግስት ጀምሮ ነው። ነገር ግን አሁን በስልጣን ላይ ያለው የኦሮሞ ብልጽግና መንግሥት የወልቃይትን ህዝብ ፍትሃዊ ጥያቄ እንደ ስልጣን ማራዘሚያ ስልት በመጠቀም በአማራና በትግራይ ህዝብ መካከል ግጭት መፍጠሪያና የህዝብ እልቂት ማካሄጃ መሳሪያ አድርጎ በመጠቀም ላይ እንደሚገኝ በሁሉም ዘንድ ግልፅ እየሆነ መጥቷል።

በተለይም በአሁኑ ወቅት የኦሮሞ ብልፅግና መንግሥትና ትህነግ/ወያኔ ሆን ብለው የፕሪቶሪያውን ስምምነት እንደ ሽፋን በመቁጠርና በአማራ ክልል ውስጥ ያለውን አለመረጋጋት እንደ ጥሩ አጋጣሚ በመጠቀም የወልቃይት፣ ጠገዴ፣ ጠለምትና፣ ራያን ጉዳይ እንደ አዲስ እያራገቡትና የአማራን ህዝብ ወደ በለጠ አለመረጋጋትና ቁጣ እየገፉት ይገኛሉ። ስለሆነም በዚህ መግለጫ ስማችን የተካተትን ተቋማት የሚከተሉትን ግልፅ መልዕክቶች፣ ማሳሰቢያዎችና፣ ማስጠንቀቂያዎች ለህዝባችንና ለሚመለከታቸው አካላት እናስተላልፋለን።

### <u>1ኛ. ለኢትዮጵያ ፌደራላዊ መንግስት</u>

የአማራ ህዝብ የማንነት ጥያቄ ያነሳባቸው ወልቃይት፣ ጠገዴ፣ ጠለምትና፣ ራያ ከህገ-መንግስቱ መፅደቅና ከፌደራል ስርአቱ መዋቀር በፊት እንደሆነ መንግስት በተደጋጋሚ በአደባባይ የገለፀው እውነታ ነው። ስለሆነም የወልቃይት፣ ጠገዴ፣ ጠለምትና፣ ራያ፣ ጉዳይ የሚፈታው በፖለቲካ ውሳኔ መሆኑ ለማንም ግልፅ ነው።

ነገር ግን መንግስት ለህዝብ ፍትሃዊ ጥያቄ በወቅቱ ምላሽ መስጠት ሲገባው ጥያቄውን እጅግ ከሚገባው በላይ እያጓተተው እንደሚገኝ እንረዳለን። ይልቁንም ወቅት እየጠበቀ ጥያቄውን እንደ አዲስ በማራገብ በትግራይና በአማራ ህዝብ መካከል አላስፈላጊ ውጥረትና ሽብር በመንዛት ላይ ይገኛል።

ስለሆነም መንግስት በአሁኑ ሰአት እየተከተለ የሚገኘውን በህዝቦች መካከል ጦርነትንና ግጭትን የመፍጠር ድርጊቱ እንዲቆጠብና የወልቃይት፣ ጠገዴ፣ ጠለምትና፣ ራያ ህዝብ የአማራ ማንነት በአፋጣኝ እውቅና እንዲሰጥ ስንል እንጠይቃለን። ከዚህ እኩይ ድርጊቱ የማይቆጠብና ሀገርን ወደ ከፋ አዘቅት የሚወስድበትን መንገድ በአፋጣኝ የማይገታ ከሆነ ከህዝባችንና ከዓለም ዓቀፉ ማህበረሰብ ጋር በመሆን ሀገር የማዳን ዘመቻ ውስጥ ለመግባት የምንገደድ መሆኑን ከወዲሁ ማሳሰብ እንወዳለን።

## 2ኛ. ለመላው የኢትዮጵያ ህዝብ

ከቅድመ-አክሱም ጀምሮ እስከ 1983 ዓ.ም ወልቃይት-ጠገዴና ጠለምት ከበጌምድር ስሜን ግዛት ተነጥለው አያውቁም፡፡ በአስተዳደራዊ ታሪክ ደረጃ የወልቃይት፣ ጠገዴ፣ ጠለምት ታሪክ ከበጌምድር ስሜን ታሪክ የማይነጠል የተጋመደ ታሪክ አለው። ይህን የአስተዳደራዊ ታሪክ በማስረጃ ህግ መመዘኛ መስፈርቶች ማለትም ገለልተኝነት፣ ተዓማኝነት፣ የእውነታ ይዞታ እና አግባብነትን መሰረት በማድረግ የተለያዩ የአገር ውስጥ እና የውጭ ጸሐፊዎች፣ አሳሾች፣ የመንግስታት ቆንስሎች ዲፕሎማቶች፣ የሀይማኖት ሰባኪዎች ሚስዮናዊያን እና የነገሥታት ዜና መዋዕል ጸሐፊዎች ከቅድመ-አክሱም ዘመነ መንግሥት እስከ 1983 ዓ.ም. ድረስ ያሉትን ታሪካዊ ማስረጃዎችን መሰረት አድርገን ስንመለከተው አካባቢዎቹ የበጌምድር-ጎንደር አካል ዐማራ ለመሆናቸው ጥርጥር የለውም፡፡

የትግራይ ክፍለ ሃገር ገዢ የነበሩት የትግራይ ተወላጅ ልዑል ራስ መንገሻ ሥዩም በሰጡት ምስክርነት፣ ወልቃይት፣ ጠገዴ፣ ጠለምት፣ ራያ፣ በትግራይ ክፍለ ሃገር ተስተዳድረው እንደማያውቁና የአማራ ግዛቶች እንደነበሩ አረጋግጠዋል። ጠ/ሚ አብይ አህመድም ቢሆን በተደጋጋሚ ወልቃይት፣ ጠገዴና፣ ጠለምት የጎንድር/በጌምድር አካል እንደሆኑና ህዝቡም አማራዊ ማንነቱን ለማስከበር ለዘመናት ሲታገል እንደቆየ ማረጋገጫ ሰጥተዋል።
የወልቃይት ሕዝብ ጥያቄ የፍትህ ጥያቄ ነው! የወልቃይት ሕዝብ ጥያቄ ለኢትዮጵያ አንድነትና ሉዓላዊነት የተከፈለ የ 40 ዓመታት ሰቆቃና ግፍ መቋጫ ጥያቄ ነው! የወልቃይት ጥያቄ ኢትዮጵያ ሀገራችን በትህነግ/ወያኔ ለተቀበለችው መከራና ፍዳ ሁሉ መቋጫ ጥያቄ ነው! የወልቃይት ጥያቄ የኢትዮጵያ ህልውና ጥያቄ ነው!

የወልቃይት ሕዝብ ፍትሃዊ ጥያቄ የመንግሥት እድሜ ማራዘሚያና በህዝቦች መካከል ግጭት ከመፍጠሪያነት ወጥቶ በአፋጣኝ ግልፅና ፍትሃዊ ምላሽ ሊያገኝ ይገባል። ስለሆነም መላው ፍትህና ሰላም ወዳድ የሆንከው የኢትዮጵያ ህዝብ ከወልቃይት፣ ጠገዴ፣ ጠለምትና፣ ራያ ሕዝብ ፍትሃዊ ጥያቄ ጎን በመቆም ህዝባችን ፍትህ እንዲያገኝ በመንግሥትና በውሳኔ ሰጭ አካላት ላይ ጫና እንድትፈጥር ጥሪ እናቀርብልሃለን።

## 3ኛ. ለመላው የአማራ ህዝብ

በአሁኑ ሰአት የአማራ ህዝብ ከጫፍ እስከ ጫፍ በጦርነት ውስጥ እንደሚገኝ ለማንም ግልፅ ነው። የአማራን ህዝብም ሆነ ክልሉን የሚያስተዳድር በህዝብ የተመረጠ አካል የለም። ዛሬ ህዝባችን በአስቸኳይ ጊዜ አዋጅና በኮማንድ ፖስት ጭፍለቃ እጅ-ከወርች ታስሮ እየተሰቃየ የሚገኝበት የሰቀቃ ወቅት ነው።

የወልቃይት ጥያቄ የአማራ ወጣቶች “ወልቃይት ብረሳሽ ቀኜ ትርሳኝ” እያሉ ደረታቸውን ለፋሽስቱ ትህነግ/ወያኔ የጥይት አረር የሰጡለት የፍትህ ጥያቄ ነው! ወልቃይት ለአማራ ሕዝብ የሕልውና ትግል ግብ መድረስ አስፈላጊነቱ ወሳኝ እውነታዎች፣ የጂኦግራፊ አቀማመጡና የተፈጥሮ ሃብት ምንጩ ነው። ወልቃይት ለአማራ ህዝብ ለፋሽስቶችና ለወራሪዎች አገዛዝ የአልምበረከክም ባይነቱ ማረጋገጫ ምሳሌ ነው! ለመላው የዐማራ ሕዝብ የመኖርና ያለመኖር መገለጫ ነው። ያለ ወልቃይት አማራነት የለም!

በአንፃሩ ደግሞ የአማራን ህዝብ ፍትሃዊ የማንነት ጥያቄዎች ለመመለስ ፈቃደኛ ያልሆነው የጠቅላይ ሚኒስተር አብይ መንግሥት “በእንቅርት ላይ ጆሮ ደግፍ” እንዲሉ በጦርነት የሚያምሰውን ህዝብ ወልቃይት፣ ጠገዴ፣ ጠለምትና፣ ራያን፣ ሰበብ በማድረግ ወደ ሌላ ዙር ጦርነት ለማስገባት ነጋሪት እየጎሰመ ይገኛል።

በመሰረቱ የፕሪቶሪያ ስምምነት ትህነግ/ወያኔ በጦርነት ተንበርክኮና ሱሪውን አውልቆ እራሱን ከፈፅሞ መደምሰስ ለማዳንና ትጥቁን አስረክቦ በሰላም ለመኖር የፈረመው የተሸናፊዎች የውርደት ውል እንጂ በወልቃይት፣ ጠገዴ፣ ጠለምትና፣ ራያ ህዝብ የአማራ ማንነት ጥያቄ ላይ የመፍትሔ መመሪያ ሊሆን የተፈረመ ውል አይደለም። ውሉ የተፈረመው በብልፅግና መንግሥትና በትህነግ/ወያኔ መካከል እንጂ የአማራን ህዝብ አይወክልም።

ትህነግ/ወያኔ ያለጦርነት መኖር እንደማይችል በተደጋጋሚ ከድርጊቶቹ መገንዘብ እንችላለን። አሁንም ወልቃይትንና ራያን በኃይል ለመቆጣጠር ትንኮሳ እያደረገ ይገኛል። በአንፃሩ ደግሞ አሁን በስልጣን ያለው የኦሮሞ ብልጽግና መንግሥት፣ የወልቃይት፣ ጠገዴ፣ ጠለምት፣ ራያ፣ የማንነት ጥያቄዎችን ከመመለስ ይልቅ፣ አማራንና ትግሬን በማጋጨት ብሎም በማዳከም ስልጣኑን ለማራዘም እየተጠቀመበት ይገኛል።

እነዚህን አካባቢዎች ለትህነግ/ወያኔ ወራሪ ሃይል አሳልፎ መስጠት ማለት፣ መላው አማራ ከትውልድ እስከ ትውልድ በማያባራ ከዚህ ቀደሙ በከፋ ጭፍጨፋ ውስጥ ይውደቅ ብሎ እንደመፍረድ ነው። ስለሆነም መላው የአማራ ሕዝብ በተለይም የወልቃይት፣ የጠገዴ፣ የጠለምት፣ የራያ፣ ሕዝብ ከመቸውም በላይ መስዋዕት ተከፍሎበት ከእጁ የገባውን ማንነቱንና ዕርስቱን ላለማስነጠቅ፣ ሰብዓዊና ዲሞክራሲያዊ መብቱን ዳግም ላለማስጨፍለቅና፣ እንደ አማራ ህዝብና እንደ ኢትዮጵያዊ ዜጋ በክብርና በኩራት ለመኖር አስፈላጊውን እርምጃ ለመውሰድ ዝግጁ መሆን ይጠበቅበታል።

**4ኛ. ለመላው የትግራይ ህዝብ በተለይም ለትግራይ ልሂቃን**

ትህነግ/ወያኔ ያለጦርነት መኖር እንደማይችል በተደጋጋሚ ከድርጊቶቹ መገንዘብ እንችላለን። ለዚህም ነው የትህነግ/ወያኔ እስትንፋሱ ሰላም ሳይሆን ጦርነት ነው የምንለው። የትግራይን ህዝብ ለከፋ ጦርነት የዳረገውና ከወገኖቹ ጋር በሰላም እንዳይኖር እያደረገው የሚገኘው ይኸው ትህነግ/ወያኔ የሚከተለው የእብሪትና የጦረኝነት ባህሪ ነው።

ከታሪክ እንደምንረዳው የጎንደርም ሆነ የወሎ ህዝብ ከትህነግ/ወያኔ መፈጠር በፊት ከትግራይ ህዝብ ጋር አንድም ግዜ በጦርነት ውስጥ ገብቶ አያውቅም። ወልቃይት፣ ጠገዴና፣ ጠለምት ህዝብና ዕርስቶቹ የጎንደር ታሪካዊ መሬቶች መሆናቸው ብቻ ሳይሆን በትግራይና በጎንደር መካከል ተከዜን የመሰለ ከዘመን ጋር የማይለወጥና የማያረጅ ተፈጥሯዊ ወሰን እንዳለ ከእናንተ የተሰወረ አይደለም። የወሎ ህዝብና መሬቶች የሆኑት ራያ፣ ወፍላ፣ አላማጣ እንዲሁ የትግራይ ጥሩ ጎረቤቶች እንጂ የትግራይ አካል ሆነው አያውቁም። ይህን ጣፋጭ እውነት አስረግጠው ከተናገሩት ከልዑል ራስ መንገሻ ሥዩም የተሻለ ምስክርም ሆነ እሳቸው ከፃፉት መፅሐፍ የሚልቅ የቅርብ ማስረጃ የለም።

ትህነግ/ወያኔ ወልቃይትን፣ ጠገዴንና፣ ጠለምትን በወረራ ከያዘበት እለት ጀምሮ ህዝባችን የተፈጸመበትን ሰቆቃ በመቃወም ነፍጥ አንስቶ ለህልውናው ሲታገል እንደነበር እውነታው ከእናንተ የተሰወረ አይደለም። ትህነግ/ወያኔ መንግስት ከሆነም በኃላ ህዝባችን የአማራ ማንነቴ ይከበርልኝ በማለት በሰላማዊ መንገድ ያደረገውን ትግል የትግራይ ልሂቃን ጠንቅቃችሁ ታውቃላችሁ። ነገር ግን የትህነግ/ወያኔ እብሪትና የጦርነት አባዜ ለህዝባችን ጥያቄ ሰላማዊ መፍትሄ ከመስጠት ይልቅ ጉዳዩ በጦርነት እንዲቋጭ አስገድዶታል። በዚህም ጦርነት በትግራይም ይሁን በአማራ ህዝብ በኩል ክቡር የሆነው የወገኖቻችን ህይወት በከንቱ ጠፍቷል።

ዛሬ የወልቃይት፣ የጠገዴ፣ የጠለምትና፣ የራያ ህዝብ በልጆቹ እየተመራ በአንፃራዊ ሰላምና እፎይታ ውስጥ ይገኛል። የሚያስተዳድሩትም የሕዝባችን ከትግራይ ህዝብ ጋር ሰላምና ጥሩ ወንድማማችነት እንጂ ጦርነት አይፈልጉም። ለዚህም ነው ሰላማዊ የትግራይ ተወላጆችን በውስጡ አቅፎና ደግፎ እየኖረ የሚገኘው። ህዝባችን ለ43 ዓመታት የተጠማውን ሰላምና እድገት በራሱ ተነሳሽነት እንደ አይኑ ብሌን እየጠበቀ የሚገኘው።

በአንፃሩ ደግሞ ጦርነት ሱሱ የሆነው ትህነግ/ወያኔ በብዙ መቶ ሺዎች ያስጨረሳቸውን የትግራይ ወጣቶች መርዶ ለወላጆቻቸው ተናግሮ ሳይጨርስ አሁንም ወልቃይትንና ራያን በኃይል ለመውረር የጦርነት ከበሮ እየደለቀና ትንኮሳ እያደረገ ይገኛል።

በእኛ እምነት ትህነግ/ወያኔ ለትግራይ ህዝብ ያተረፈለት ልማትና ሰላም ሳይሆን ጥላቻና እልቂት ነው ብለን እናምናለን። ይህም የሆነው በትህነግ የተሳሳተ ተፈጥሯዊ ማንነትና ከጅምሩ የተሳሳተ አካሄድ ነው ብለን እናምናለን። ከዚህም በመነሳት ትህነግ/ወያኔ ለመኖር ሲል ወደ

ጦርነት ይገባል የሚል ጥርጣሬ አለን። ስለሆነም ይህ እብሪተኛና ጦርነት ናፋቂ ቡድን ከልካይና ተቆጪ አጥቶ ወደ ሙሉ ጦርነት ከገባ ግን ካሁን ቀደም ካየነው የሕይወትና ንብረት ውድመት የከፋውን ጥፋት ሊያስከትል ይችላል ብለን እንሰጋለን።

ስለሆነም የትግራይ ሕዝብ በተለይ ልሂቃኑ የትህነግ/ወያኔ ጠብ አጫሪነት ሊያወግዘውና ለሰላምና ለፍትሕ ዘብ ሊቆም ይገባል ብለን እናምናለን። ነገር ግን እንደ ከዚህ ቀደሙ ትህነግ/ወያኔን እየተከተሉ የጦርነት ከበሮ በመደለቅና ህዝብ ወደ እሳት በመማገድ ትልቅ ሚና የነበራቸው ምሁራን በዚሁ ከቀጠሉ፣ ከተጠያቂነት እንደማያመልጡ ማወቅ አለባቸው። በዝምታ ድጋፍ መስጠትና የጥፋቱ ተባባሪ መሆን ከታሪክና ከትውልድ ተጠያቂነት አያድንም።

**<u>5ኛ. ለመላው የወልቃይት፣ የጠገዴ፣ የጠለምትና፣ የራያ ህዝብ</u>**

ሰላምና ነፃነት ወዳዱ የወልቃይት፣ የጠገዴ፣ የጠለምትና፣ የራያ ህዝብ ሆይ! ከረዥም ዘመናት ትግልና ህልቆ መሳፍርት ከሌለው መስዋዕትነት በኋላ ነፃነትህን ከእጅህ አስግብተሃል። ይሁን እንጂ ወራሪውና ፋሽስቱ ትህነግ/ወያኔ በአለፉት ጥቂት የነፃነት አመታት ያጣጣምከውን ሰላም፣ ልማትና፣ እድገት ሊነጥቅህና ዳግም ዘርህን ሊያጠፋ፣ ሚስትህንና ሴት ልጅህን ሊደፍር፣ ወጣቶችህን በጅምላ ሊያሰቃይና ሊጨፈጭፍ፣ ንብረትህን ሊዘርፍና ከዕርስትህ ሊያፈናቅልህ የጦርነት ነጋሪት እየጎሰመና ሾተሉን እየሳለ ይገኛል።

ሰላምና ነፃነት በችሮታ ከጨቋኞች የሚሰጥ ወይም በምኞት ከገዥዎች ወንበር የሚገኝ ሳይሆን በጀግኖች ደምና አጥንት መስዋዕትነት የሚጎናፀፉት፣ የሚጠብቁት፣ የሚያፀኑት ክቡር የተፈጥሮ ፀጋ መሆኑን ከአንተ በላይ ማንም አስረጂ አይገኝም። ስለሆነም በክቡር መስዋዕትነት የተጎናፀፍከውን ማንነትህንና ነፃ ያወጣኸውን ዕርስትህን ዳግም ለትህነግ/ወያኔ ወረራ አሳልፈህ እንዳትሰጥ ነቅተህ ጠብቅ።

# ፍትህ፣ ሕልውናው አደጋ ላይ ለወደቀው የአማራ ሕዝብ!

**ሚያዝያ 4 ቀን 2016 ዓ.ም.**